EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

# የመረጃ ክፍለ-ጊዜ፡- የልጅ እድገት ተቋም የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመርን መጠቀም

ጁን 2023

OSSE

WE ARE WASHINGTON DC
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# እንኳን ወደ የልጅ ኢድገት ተቋም መሪዎች በደህና መጡ!



EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

OSSE

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# የዙም ተሳትፎ

ቀድመው መውጣት ይፈልጋሉ? በማንኛውም ጊዜ **ከስብሰባ ይውጡ** የሚለውን አዝራርን ይጫኑ።

ጥያቄዎችዎን የ Q&A feature (**የጥያቄና መልስ ምርጫን**) በመጠቀም ያስገቡ።




ወደ **መገልገያ ጽሁፎች** የሚወስዱ ተጨማሪ **መረጃዎች** እና **ማስፈንጠሪያዎች** እዚህ ይጋራሉ።

ምርጫዎ በሆነ ቋንቋ ስብሰባውን ያዳምጡ። **የአማርኛ** ወይም **የስፓኒሽ አስተርጓሚን** ለማግኘት እዚህ ይጫኑ።

# በቀጥታ የሚተላለፉ ጥያቄዎች እና መልሶች







ጥያቄዎን እዚህ ይጻፉ እና ያስገቡ የምለውን ይጫኑ።

# የዛሬ ተናጋሪዎች ጋር ተዋወቁ

- **Eva Laguerre፣** የቅድመ ትምህርት ጊዜያዊ ምክትል ተቆጣጣሪ፣ የኦፊስ ኦፍ ዘ ስቴት ሱፐርኢንተንደንት ኦፍ ኤጁኬሽን
- **Hannah Matthews፣** የፖሊሲ፣ እቅድ እና ምርምር ዳይሬክተር፣ OSSE





# አጀንዳ

1. የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ በጀት አመት 2024 (FY24) እንዴት እንደሚሰራ
2. የልጅ እድገት ተቋም (CDF) የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር እና ዝቅተኛ ደመወዞች አጭር መግለጫ
3. የተቋም CDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማትን ማስላት
4. Q&A
5. መዝጊያ እና ቀጣይ ደረጃዎች

OSSE GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፍ

# የ FY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ እኩልነት የገንዘብ ድጋፍ

- በFY24፣ OSSE በልጅ እድገት ተቋም (CDF) የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር አማካኝነት ለቅድመ አስተማሪዎች ማካካሻን ለመጨመር የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፎችን በቀጥታ ለልጅ እድገት ተቋማት ያሰራጫል።
- የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ከአሁን በኋላ በAidKit በኩል በቀጥታ ክፍያዎችን አያገኙም።



# የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ

- ከ CDF የደመወዝ ክፍያ ግንዝብ ቀመር ገንዘቦችን ለመቀበል፣ የልጅ እድገት ተቋማት በOSSE ፍቃድ የተሰጣቸው እና ብቁ ለሆኑ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች፣ በሥራ መደብ እና በዲግሪ፣ በOSSE ለ FY24 የተቋቋመውን ዝቅተኛ ደመወዝ የሚያሟሉ ወይም የሚበልጡ ደሞዞችን ለመክፈል መስማማት አለባቸው፣
- መሳተፍ አማራጭ ነው ግን በጣም የሚበረታታ ነው።
- ለመሳተፍ የሚፈልጉ የልጅ እድገት ተቋማት በOSSE በተሰየመ ሂደት አማካኝነት ወደ ፕሮግራሙ መርጠው መግባት አለባቸው።
  - በዚህ ሂደት ላይ ተጨማሪ መረጃ በዚህ በጋ ከልጅ እድገት ተቋማት ጋር የሚጋራ ይሆናል።

# የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ

- የCDF የደመወዝ ክፍያ ቀመር ሽልማቶች ለሚከተሉት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡-
  - ለመሪ እና ረዳት አስተማሪዎች ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶችን ለማሟላት።
  - ለተጨማሪ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች እና ሌሎች የልጅ እድገት ተቋም ሰራተኞች የሰራተኞች ደመወዝ ወይም ማካካሻ ለመክፈል።
  - ለቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች እና ሌሎች የልጅ እድገት ተቋም ሰራተኞች የጤና ውጪዎች እና ሌሎች ተጨማሪ ጥቅማጥቅሞችን ለመክፈል።
  - ዝቅተኛውን የደመወዝ መስፈርቶች እና/ወይም ከቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ የOSSE መስፈርቶችን ጋር የተያያዙ አስተዳደራዊ ወጪዎችን ለመክፈል።
  - ለህጻናት የእንክብካቤ እና የቅድመ ትምህርት አገልግሎቶችን ከመስጠት ጋር የተያያዘውን የተቋሙ ቀጥተኛ የስራ ማስኬጃ ወጪዎችን ለመክፈል።

# የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር እና ዝቅተኛ ደመወዞች

# የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር

- የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር በ FY24 በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ውስጥ ለመሳተፍ በመረጡ የልጅ እድገት ተቋም ሰራተኞች የሚደርሰውን የክፍያ መጠኖች ለመወሰን ጥቅም ላይ የሚውል ቀመር ነው።
- የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር የተዘጋጀው በቅድመ ልጅነት ትምህርት ፍትሃዊ የማካካሻ ግብረ ሃይል ምክረ ሃሳቦች እና፣ በOSSE ቅድመ ትምህርት ፍቃድ መስጫ መሳሪያ (DELLT)፣ በ2022 የዲሲ የልጅ እንክብካቤ የአቅራቢዎች ዳሰሳ፣ የOSSE 2023 የወጪ ሞዴል ትንተና ውስጥ ያለውን የተቋም ተኮር ውሂብ እና ከውጪ ባለድርሻ አካላት የተገኘ ግብአትን ጨምሮ ከበርካታ ምንጮች የተገኘው ውሂብ መሰረት በማድረግ ነው።

# FY24 CDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር

| መሰረታዊ ሽልማት | | አስተዳደራዊ እድገት | | የፍትሃዊነት ማስተካከያ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አሁን ባሉት ደመወዞች እና በዝቅተኛ ደመወዞች መካከል ያለው ልዩነት በሚና እና በFTE የትምህርት ማስረጃ | + | ከመሰረታዊ ሽልማት 15 በመቶ | + | እስከ 40 በመቶ የሚሆነው የመሰረታዊ ሽልማት እንደ ፈቃድ እንደተሰጠው አቅም ድርሻ ይወሰናል | = | የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት |

# ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶች

| ሚና | የትምህርት ማስረጃዎች | የFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች (አመታዊ ደመወዝ) | የFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች (የሰዐት ደመወዝ) |
|---|---|---|---|
| ረዳት አስተማሪ | ከልጅ እድገት ተባባሪ (CDA) ያነሰ | $43,865/አመት | $21.09/ሰዐት |
| | CDA | $51,006/አመት | $24.52/ሰአት |
| | ተባባሪ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ | $54,262/አመት | $26.09/ሰአት |
| መሪ መምህር | CDA | $54,262/አመት | $26.09/ሰአት |
| | ተባባሪ ዲግሪ | $63,838/አመት | $30.69/ሰአት |
| | የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ | $75,103/አመት | $36.11/ሰአት |

- ከCDF የደመወዝ ክፍያ ቀመር የገንዘብ ድጋፍ የሚቀበሉ የልጅ እድገት ተቋማት ለረዳት መምህራን እና ለመሪ መምህራን በOSSE ከተመሰረተው ዝቅተኛውን ደመወዞች የሚያሟሉ ወይም የሚበልጡ ደመወዞችን መክፈል አለባቸው።
  - ረዳት መምህር = ረዳት መምህር፣ ሞንቴሶሪ ረዳት መምህር፣ የ PKEEP ረዳት መምህር፣ ተባባሪ የቤት ተንከባካቢ
  - መሪ መምህር = መምህር፣ የሞንቴሶሪ መምህር፣ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ፣ የተስፋፋ የቤት ተንከባካቢ
- ዝቅተኞቹ የደመወዝ ክፍያዎች ለሙሉ ጊዜ፣ አመቱን ሙሉ ለሚሰሩ ሰራተኞች ያስፈልጋሉ።
- የትርፍ ሰአት ወይም የትርፍ አመት ስራ ከሚሰሩ ሰራተኞች ጋር የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራሞች ከተዘረዘሩት የሰዐት ደመወዞች ጋር ተመጣጣኝ ወይም ከዚያ የሚበልጡ የሰዐት ደመወዞችን መክፈል አለባቸው።

# ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶች

- የሚፈለገው ዝቅተኛ ደመወዝ እና ተጓዳኝ የደመወዝ ማሚያ በከፍተኛ የትምህርት ማስረጃ ወይም በአስተማሪ በተሰጠው ዲግሪ ላይ የሚመሰረት ይሆናል።
- **ለመሪ መምህራን፡-**
  - ለ“BA” የደመወዝ ማሚያ ብቁ ለመሆን፣ የቅድመ ልጅነት ትምህርት (ECE) የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም በ ECE ውስጥ ከ24 የትምህርት ሰአታት በላይ ወይም እኩል የሆነ የመጀመሪያ ዲግሪ (ወይም ከዚያ በላይ) ይኑርዎት።
  - ለ“AA” የደመዝ ማሚያ ብቁ ለመሆን፣ በ ECE ውስጥ ተባባሪ ዲግሪ ወይም ከ24 የትምህርት ሰዐታት የሚበልጥ ወይም እኩል የሆነ ተባባሪ ዲግሪ ይኑርዎት።
  - ለ“CDA” የደመወዝ ማሚያ ብቁ ለመሆን፣ CDA ወይም በECE ውስጥ ከ15 ሰዐታት በላይ ወይም እኩል የሆነ 48 የትምህርት ሰአታት ይኑርዎት።
- **ለረዳት መምህራን፡-**
  - ለ“AA” የደመወዝ ማሚያ ብቁ ለመሆን፣ የተባባሪ ዲግሪ (ወይም ከዚያ በላይ) ይኑርዎት።
  - ለ“CDA” የደመወዝ ማሚያ ብቁ ለመሆን፣ CDA ይኑርዎት።
  - ከ “CDA ላነሰ” የደመወዝ ማሚያ ብቁ ለመሆን፣ ከCDA ያነሰ ይኑርዎት።

# ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶች

- የልጅ እድገት ተቋማት በቋሚ ደመወዝዎች ወይም ደመወዝዎች ዝቅተኛውን የደመወዝ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።
- የልጆች እድገት ተቋማት በአንድ ጊዜ ጉርሻዎች ወይም በአጠቃላይ ድምር ክፍያዎች መስፈርቶቹን ላያሟሉ ይችላሉ።
- የCDF የደመወዝ ክፍያ ቀመር የገንዘብ ድጋፎችን ያልተቀበሉ ተቋማት ለሰራተኞቻቸው የሚፈለገውን ዝቅተኛ ደመወዝዎች እንዲከፍሉ አይገደዱም ነገር ግን የ2016 የፍትሃዊ እድል ዝቅተኛ የደሞዝ ህግ እና በዲስትሪክቱ የልጅ እንክብካቤ ድጎማ ፕሮግራም ውስጥ ለሚሳተፉ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች፣ የ2006 የኑሮ ደሞዝ ህግን ጨምሮ ከሌሎች የዲስትሪክት እና/ወይም የፌደራል ህጎች እና ለሁሉም ቀጣሪዎች ተፈጻሚ የሚሆኑ የሰራተኛ ደመወዞችን እና ሰዐታትን የሚመለከቱ መስፈርቶችን ማክበር አለባቸው።

# የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመርን መከፋፈል

# የ CDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር እንዴት ይሰራል?

እያንዳንዱ የ CDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር አካል ለአንድ የግል የልጅ እድገት ተቋም በየሩብ አመቱ ይሰላል።

**መሰረታዊ ሽልማት**

አሁን ባሉት ደመወዞች እና በዝቅተኛ ደመወዞች መካከል ያለው ልዩነት በሚና እና በFTE የትምህርት ማስረጃ

\+

**አስተዳደራዊ እድገት**

ከመሰረታዊ ሽልማት 15 በመቶ

\+

**የፍትሃዊነት ማስተካከያ**

እስከ 40 በመቶ የሚሆነው የመሰረታዊ ሽልማት እንደ ፈቃድ እንደተሰጠው አቅም ድርሻ ይወሰናል

=

**የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት**

# መሰረታዊ ሽልማት እንዴት ይሰላል?

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የመምህራን ብዛት – CDA | × | የደመወዝ ማሟያ መምህር – CDA | = | መሰረታዊ ሽልማት |
| የመምህራን ብዛት– AA | | የደመወዝ ማሟያ መምህር– AA | | |
| የመምህራን ብዛት– BA | | የደመወዝ ማሟያ መምህር– BA | | |
| የረዳት መምህራን ብዛት – ከ CDA በታች | | የደመወዝ ማሟያ ረዳት መምህር – ከ CDA በታች | | |
| የረዳት መምህራን – CDA | | የደመወዝ ማሟያ ረዳት መምህር – CDA | | |
| የረዳት መምህራን – AA | | የደመወዝ ማሟያ –ረዳት መምህር AA | | |

- መሰረታዊ ሽልማቱ የሚሰላው በአንድ ተቋም ውስጥ ያሉትን የመምህራን ብዛት፣ በሚና እና በትምህርት ማስረጃ ወይም በዲግሪ መሰረት በማድረግ፣ በተጓዳኝ የደመወዝ ማሟያ በማባዛት እና ጠቅላላውን በመደመር ነው።
- የመምህራን ብዛት እና የትምህርት ማስረጃ ደረጃዎች በቅድመ ትምህርት ፈቃድ መስጫ መሳሪያ ክፍል (DELLT) ውስጥ ባለው ተቋም ሪፖርት በተደረገው የሰራተኞች አቅርቦት ውሂብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

# የደመወዝ ማሟያ ምንድን ነው?

| ሚና | የትምህርት ማስረጃዎች | የFY24 የደመወዝ ማሟያ (አመታዊ) |
|---|---|---|
| ረዳት አስተማሪ | ከ CDA ያነሰ | $2,329 |
| | CDA | $9,470 |
| | ተባባሪ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ | $12,726 |
| መሪ መምህር | CDA | $8,503 |
| | ተባባሪ ዲግሪ | $18,079 |
| | የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ | $29,344 |

- የደመወዝ ማሟያ በአማካኝ ደመወዝ እና ለአስተማሪ በሚና እና በትምህርት ማስረጃ መሰረት ለአንድ መምህር በሚሰጠው ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርት መካከል ያለው ልዩነት ነው።
- አማካይ የመምህር ደመወዝ በ2022 የልጅ እንክብካቤ አቅራቢ ዳሰሳ ጥናት ላይ በተሰጡ ምላሾች ላይ የተመሰረተ ነው።
- ለእያንዳንዱ ሚና የደመወዝ ማሟያ የተወሰነ መጠን ነው።

# የአስተዳደር ማሻሻያው እንዴት ይሰላል?

- የአስተዳደር ማሻሻያው የመሰረታዊ ሽልማት 15 በመቶ ነው።
- ለተቋሙ የግዴታ የደመወዝ ክፍያ ግብሮች እና ሌሎች ሊሆኑ የሚችሉ ተጨማሪ ወጪዎችን ለመጨመር የገንዘብ ድጋፎችን ይሰጣል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መሰረታዊ ሽልማት | ✖ | 15 በመቶ | = | አስተዳደራዊ እድገት |

# ፍትሃዊ ማስተካከያ እንዴት ይሰላል?

- የፍትሃዊነት ማስተካከያው ከመሰረታዊ ሽልማቱ እስከ 40 በመቶ ይደርሳል፣ ይህም በተቋሙ ድጎማ ምዝገባ ላይ ፈቃድ እንደተሰጠው አቅም ድርሻ ላይ የተመሰረተ ነው።
- ቤተሰቦችን እና አነስተኛ ኢኮኖሚያዊ ሃብቶች ያላቸውን ማህበረሰቦችን ለሚያገለግሉ የልጅ እድገት ተቋማት የተጨመረ የገንዘብ ድጋፍን ይመራል።
- በልጅ እንክብካቤ ድጎማ ፕሮግራም ውስጥ የማይሳተፉ ተቋማት በመሰረታዊ ሽልማታቸው ላይ ፍትሃዊነት ማስተካከያዎችን አያገኙም።

የድጎማ ምዝገባ ÷ ፈቃድ ያለው አቅም × መሰረታዊ ሽልማት × 40 በመቶ = የፍትሃዊነት ማስተካከያ

# የተቋም CDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማትን ማስላት

# ለምሳሌ፣ የልጅ እድገት ማዕከል

- አንድ የልጅ እድገት ማዕከል በFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ለመሳተፍ ከOSSE ጋር ስምምነት አደረገ። በDELLT ውስጥ ባለው ተቋም የቀረበው መረጃ የሚከተለውን ያሳያል፡-
  - ማዕከሉ **ስምንት** መሪ መምህራንን ቀጥሯል
    - በቅድመ ልጅነት ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 2 መምህራን
    - በቅድመ ልጅነት ትምህርት ተባባሪ ዲግሪ ያላቸው 4 መምህራን
    - CDAዎች ያላቸው 2 መምህራን
    - ማዕከሉ **ስድስት** ረዳት መምህራንን ቀጥሯል
    - በቅድመ ልጅነት ትምህርት AA ያላቸው 2 ረዳት መምህራን
    - CDAዎች ያሏቸው 2 ረዳት መምህራን
    - ከCDA ያነሰ ያላቸው 2 ረዳት መምህራን
  - ማእከሉ 52 ህጻናትን የመያዝ ፈቃድ ያለው አቅም አለው።
- በተጨማሪ፣ ከድጎማ ስርዐቱ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ተቋሙ የልጅ እንክብካቤ ድጎማዎችን የሚያገኙ 20 ህጻናት መዝግቧል።

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# FY24 CDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር

**መሰረታዊ ሽልማት**

አሁን ባሉት ደመወዞች እና በዝቅተኛ ደመወዞች መካከል ያለው ልዩነት በሚና እና በFTE የትምህርት ማስረጃ

+

**አስተዳደራዊ እድገት**

ከመሰረታዊ ሽልማት 15 በመቶ

+

**የፍትሃዊነት ማስተካከያ**

እስከ 40 በመቶ የሚሆነው የመሰረታዊ ሽልማት እንደ ፈቃድ እንደተሰጠው አቅም ድርሻ ይወሰናል

=

የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት

# መሰረታዊ ሽልማትን ማስላት

| | × | | = | | = |
|---|---|---|---|---|---|
| የመምህራን ብዛት – CDA (2) | × | የደመወዝ ማሟያ መምህር – CDA $8,503 | = | $17,006 | |
| የመምህራን ብዛት– AA (4) | × | የደመወዝ ማሟያ መምህር– AA $18,079 | = | $72,316 | |
| የመምህራን ብዛት– BA (2) | × | የደመወዝ ማሟያ መምህር– BA $29,344 | = | $58,688 | |
| የረዳት መምህራን ብዛት – ከ CDA በታች (2) | × | የደመወዝ ማሟያ ረዳት መምህር – ከ CDA በታች $2,329 | = | $4,658 | |
| የረዳት መምህራን – CDA (2) | × | የደመወዝ ማሟያ ረዳት መምህር – CDA $9,470 | = | $18,940 | |
| የረዳት መምህራን – AA (2) | × | የደመወዝ ማሟያ –ረዳት መምህር AA $12,726 | = | $25,452 | |

**መሰረታዊ ሽልማት**
**$197,060**

# የአስተዳደር ማሻሻያውን ማስላት

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መሰረታዊ ሽልማት | x | 15 በመቶ | = | አስተዳደራዊ እድገት |
| $197,060 | x | .15 | = | $29,559 |

# ፍትሃዊ ማስተካከያውን ማስላት

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የድጎማ ምዝገባ | ÷ | ፈቃድ ያለው አቅም | × | መሰረታዊ ሽልማት | × | 40 በመቶ | = | የፍትሃዊነት ማስተካከያ |
| 20 | ÷ | 52 | × | $197,060 | × | .4 | = | $30,317 |

# አጠቃላይ የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት

- አጠቃላይ የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት የቀመር ክፍሎች ድምር ነው።
- የሩብ አመቱ ክፍያ ከጠቅላላ ሽልማቱ 25 በመቶ ጋር እኩል ይሆናል።
- በዚህ ምሳሌ፣ የሩብ አመቱ ክፍያ ($256,936 x .25) ወይም **$64,234** ይሆናል
  - ማሳሰቢያ፥ የአንድ ተቋም የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት በየሩብ አመቱ ይሰላል

| መሰረታዊ ሽልማት | + | አስተዳደራዊ እድገት | + | የፍትሃዊነት ማስተካከያ | = | የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| $197,060 | + | $29,559 | + | $30,317 | = | $256,936 |

# ለምሳሌ፣ የልጅ እድገት ቤት

- አንድ የተስፋፋ የልጅ እድገት ቤት በFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ለመሳተፍ ከOSSE ጋር ስምምነት አድርጓል። በDELLT ውስጥ ባለው ተቋም የቀረበው መረጃ የሚከተለውን ያሳያል፡-
  - የተስፋፋው የቤት ተንከባካቢ በቅድመ ልጅነት ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ አለው።
  - ተቋሙ **ሁለት** ተባባሪ ተንከባካቢዎችን ይቀጥራል።
    - በቅድመ ልጅነት ትምህርት AA ዲግሪ ያለው 1 ተባባሪ ተንከባካቢ
    - CDA ያለው 1 ተባባሪ ተንከባካቢ
  - ማዕከሉ 9 ህጻናትን የመያዝ ፈቃድ ያለው አቅም አለው።
- በተጨማሪ፣ ከድጎማ ስርአቱ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ተቋሙ የልጆች እንክብካቤ ድጎማዎችን እንዲያገኙ 4 ህጻናትን መዝግቧል።

# FY24 CDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር

| መሰረታዊ ሽልማት | | አስተዳደራዊ እድገት | | የፍትሃዊነት ማስተካከያ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አሁን ባሉት ደመወዞች እና በዝቅተኛ ደመወዞች መካከል ያለው ልዩነት በሚና እና በFTE የትምህርት ማስረጃ | + | ከመሰረታዊ ሽልማት 15 በመቶ | + | እስከ 40 በመቶ የሚሆነው የመሰረታዊ ሽልማት እንደ ፈቃድ እንደተሰጠው አቅም ድርሻ ይወሰናል | = | የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት |

# መሰረታዊ ሽልማትን ማስላት

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የመምህራን ብዛት – CDA (0) | ✖ | የደመወዝ ማሟያ መምህር – CDA $8,503 | = | $0 | = | መሰረታዊ ሽልማት $51,540 |
| የመምህራን ብዛት– AA (0) | | የደመወዝ ማሟያ መምህር– AA $18,079 | | $0 | | |
| የመምህራን ብዛት– BA (1) | | የደመወዝ ማሟያ መምህር– BA $29,344 | | $29,344 | | |
| የረዳት መምህራን ብዛት – ከ CDA በታች (0) | | የደመወዝ ማሟያ ረዳት መምህር – ከ CDA በታች $2,329 | | $0 | | |
| የረዳት መምህራን – CDA (1) | | የደመወዝ ማሟያ ረዳት መምህር – CDA $9,470 | | $9,470 | | |
| የረዳት መምህራን – AA (1) | | የደመወዝ ማሟያ –ረዳት መምህር AA $12,726 | | $12,726 | | |

# የአስተዳደር ማሻሻያውን ማስላት

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መሰረታዊ ሽልማት | x | 15 በመቶ | = | አስተዳደራዊ እድገት |
| $51,540 | x | .15 | = | 7,731 |

# ፍትሃዊ ማስተካከያውን ማስላት

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የድጎማ ምዝገባ | ÷ | ፈቃድ ያለው አቅም | × | መሰረታዊ ሽልማት | × | 40 በመቶ | = | የፍትሃዊነት ማስተካከያ |
| 4 | ÷ | 9 | × | $51,540 | × | .4 | = | $9,163 |

# አጠቃላይ የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት

- አጠቃላይ የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት የቀመር ክፍሎች ድምር ነው።
- የሩብ አመቱ ክፍያ ከጠቅላላ ሽልማቱ 25 በመቶ ጋር እኩል ይሆናል።
- በዚህ ምሳሌ፣ የሩብ አመቱ ክፍያ ($68,434 x .25) ወይም **$17,109** ይሆናል
  - ማሳሰቢያ፥ የአንድ ተቋም የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት በየሩብ አመቱ ይሰላል

| መሰረታዊ ሽልማት | + | አስተዳደራዊ እድገት | + | የፍትሃዊነት ማስተካከያ | = | የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| $51,540 | | 7,731 | | $9,163 | | $68,434 |

# Q&A

# ተቋምዎ በ FY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ለመሳተፍ አቅዷል?

እባክዎ በማያ ላይ ለዙም ምርጫ ምላሽ ይስጡ



# መዝጊያ እና ቀጣይ ደረጃዎች



EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

OSSE

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# የልጅ እድገት ተቋም መሪዎች በቀጣይ ምን ሊጠብቁ ይችላሉ?

- በ FY24 ወደ ቅድመ ልጅነት ትምህርት ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ የመግባት ሂደት ላይ ተጨማሪ መረጃ፡፡
  - መሪዎች
  - ተጨማሪ የመረጃ ክፍለ ጊዜዎች
  - የቴክኒክ ድጋፍ
- በ FY24 ውስጥ በፕሮግራሙ ላይ ስለሚደረጉ ለውጦች ከሰራተኞች ጋር ለመነጋገር የመገልገያ ጽሁፎች

# የዛሬውን የመረጃ ክፍለ-ጊዜ ስለተካፈሉ እናመሰግናለን!

በ FY24 የቅድመ ልጅነት ትምህርት ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን የሚከተለውን ይጎብኙ፦ osse.dc.gov/fy24ecepayequity

የመገልገያ ጽሁፎች፥

- FY24 CDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር
- የFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች እና የደመወዝ መርሃ ግብር
- በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ስለ ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት ፈንድ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ ለOSSE.DELCommunications@dc.gov ኢሜይል ያድርጉ።

EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

OSSE

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DC MURIEL BOWSER, MAYOR